የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፺፬
አዲስ አበባ ሀምሌ ፳፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 94
ADDIS ABABA, 29th July, 2016

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፪/፪ሺ፰ ዓ.ም

በአፍሪካ ቀንድ ስደት የሚያስከትለው ተፅዕኖ ምላሽ እንዲያገኝ የሚያስችለው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ከዓለምአቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ..........................................ገፅ ፱፻፹፩

**<u>CONTENTS</u>**

Proclamation No. 972/2016

International Development Association Financing Agreement for Development Response to Displacement Impact project, Ratification Proclamation........................................page 9181

**አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፪/፪ሺ፰**

**<u>የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለምአቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

በአፍሪካ ቀንድ ስደት የሚያስከትለው ተፅዕኖ ምላሽ እንዲያገኝ የሚያስችለው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፸፩ ኤስ.ዲ.አር (ሰባ አንድ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) እና ፲፪ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

**PROCLAMATION No.972/2016**

**<u>A PROCLAMTION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNTAIONAL DEVELOPMENT ASSOCIAATION</u>**

**WHERE AS**, additional financing Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association provides to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount of 71,000,000 SDR (seventy one million) Special Drawing Rights for financing Development Response to Displacement Impact Project ,was signed in Addis Ababa on the 15th day of June ,2016,

**WHERE AS,** the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 26th day of July, 2016,

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በአፍሪካ ቀንድ ስደት የሚያስከትለው ተፅዕኖ ምላሽ እንዲያገኝ የሚያስችለው ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፪/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5832-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸፩ ሚሊዮን ኤስ ዲ አር (ሰባ አንድ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሀምሌ ፳፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **Short Title**

This proclamation may be cited as "International Development Association Financing Agreement for Development Response to Displacement Impact project, Ratification Proclamation No. 972/2016 ".

2. **Ratification of the Agreement**

The Financing Agreement Credit Number 5832-ET signed on 15th June, 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of 71,000,000 SDR (seventy one million) Special Drawing Rights in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of July, 2016**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**